እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ በሰላም አሸጋገራችሁ

የኢትዮጵያ ታላቁ ሀብት ባህረ ሀሳብ

ባህረ ሀሳብ የግእዝ ቃል ሲሆን ከሁለት ጥምር ቃላት የተወሰደ ሲሆን እነዚህም ባህር እና ሀሳብ ናቸው፡፡ ባህር ማለት ዘመን ማለት ነው ሀሳብ ማለት ደግሞ ቁጥር ማለት ሲሆን በአንድ ላይ የዘመን አቆጣጠር ይባላል፡፡ ባህረ ሀሳብን ለማወቅ ብዙ አባቶች ቢመኙም የመንበረ እስክንድርያ ፲፪ኛ ሊቀ ጳጳስ ለነበረው ለቅዱስ ድሜጥሮስ ተገልጾለታል፡፡ ድሜጥሮስ በሙያው ምንም አይነት የቤተክርስቲያን ትምህርት ያልነበረው በአጭር ታጣቂ፣ ነገር አዋቂ፣ ፍርድ ጠንቃቂ ገበሬ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ድሜጥሮስ የቤተክርስቲያን ትምህርት ባይኖረው ሕገ እግዚአብሔርን አክብሮ የሚኖር ስለነበር በዚህ ቅድስናው ምክንያት መልአከ እግዚአብሔር ለ፲፭ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ዩሊያኖስ ተገልጦ በነገረው መሰረት ድሜጥሮስ ፲፪ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ በመንበረ ማርቆስ ተሹሟል፡፡

ድሜጥሮስ ማለት መስታወት ማለት ነው፡፡ አባት እናቱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ደጋጎች ነበሩ፡፡ ለአካለ መጠን ሲደርስ በዘመኑ አረማውያን የበዛበት አማንያን ያነሱበት ነበርና ከአንቱ ልጅ ከልዕልተ ጋር ዳሩት፡፡ በዘመኑም የነበረው ሊቀጳጳስ ሉክዮስ ይባላል፡፡ አርጅቶ ደክሞ ነበር እና ከኔ ቀጥሎ የሚሾምላችሁን ምረጡ አላቸው፡፡ አባታችን አንተው ግብር ገብተህ ቀኖና ይዘህ ንገረን እንጂ አሉት፡፡ በቀነ ቀጥሮ አሰናበታቸው፣ በቀጠራቸው ቀን ተሰበሰቡ በሱባኤው የታዘዘ መልአክ ነግሮት ነበርና ያለ ጊዜው ያፈራች አንዲት የወይን ዘለላ ይዞ ሊባረክ ከኔ ዘንድ ይመጣል ከኔ ቀጥሎ የሚሾም እርሱ ነው አላቸው ያለውም አልቀረ ይዞ ሲመጣ እርሱን የእስክንድርያ አሥራ ሁለተኛ ሊቃነ ጳጳስ አድርጎ ሾመው፡፡ ቅዱስ ድሜጥሮስ /ከ፻፹ – ፪፻፷፪ ዓ.ም/ በመንበረ እስክንድርያ ላይ ቆይቷል፡፡ ይህም ቅዱስ አባት ቤተክርስቲያን በዘመነ ሐዲስ የምትመራበትን የአጽዋማትና የበዓላትን ቀመር ባህረ ሀሳብን የሰራ ነው፡፡ ይህ ባሕረ ሐሳብ ያለፉትን ዓመታት፤ አሁን ያሉበትን፤ ወደፊት እስከ ምጽአት የሚመጡትን አጽዋማት እና በዓላት ለማወቅ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም በዘመኑ ብዙ ድርሰቶችን መጽሐፎችን ጽፏል፡፡ በዚህ የዘመን አቆጣጠር ውስጥ የዘመነ ብሉይና የዘመነ ሐዲስ ድምር በጠቅላላው ዓመተ ዓለም ይባላል፡፡ ዓመተ ዓለም የሚሰፈርባቸው (የሚታወጅባቸው) ሰባት አዕውዳት አሉ ::

አዕዋድ የሚለው ቃል አደ ከሚል ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ዞረ ማለት ነው፡፡ አዕዋድ ማለት ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ዞሮ የሚመጣ ማለት ነው፡፡ አዕዋዳት የሚባሉት ሰባት ናቸው፡፡ እነርሱም

- **ዓውደ ዕለት**፡- ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉ ቀናት ሲሆኑ እነዚህ ቀናት በየሳምንቱ ተመላልሰው የሚመጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ሳምንታት እየተመላለሱ ወራትን ይፈጥራሉ፡፡
- **ዓውደ ወርኀ**፡- አንድ ወር የሚባለው በፀሐይ ሙሉ ሰላሳ ቀን ሲሆን በጨረቃ አንድ ጊዜ ሃያ ዘጠኝ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሰላሳ ቀን ይሆናል፡፡ ይህ በሰላሳ ቀን በየወሩ እየተመላለሰ ዓውደ ዓመትን ይሰራል፡፡
- **ዓውደ ዓመት**፡- በፀሐይ ፫፻፷፭ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስ በጨረቃ ፫፻፶፬ ቀን ከ፷፪ ኬክሮስ ነው፡፡
- **ዓውደ አበቅቴ (ንዑስ ቀመር)**፡- አስራ ዘጠኝ ሲሆን በየ፲፱ ዓመቱ ዞሮ የሚመጣ ነው፡፡ ፀሐይና ጨረቃ ተራክቦ የሚያደርጉበት ወቅት ነው፡፡
- ዓውደ ፀሐይ፡- ሃያ ስምንት ዓመት ሲሆን በየ፸፰ ዓመቱ ተመላልሶ የሚመጣ ነው፡፡ በየ፸፰ ዓመቱ ዕለቱና ወንጌላዊው ይገናኙበታል፡፡
- ዓውደ ማኅተም (ማዕከላዊ ቀመር)፡- ሰባ ስድስት ዓመት ነው፡፡ በ፸፮ ዓመት አንድ ጊዜ አበቅቴው እና ወንጌላዊው ይገናኙበታል፡፡
- ዓውደ ዐብይ ቀመር (ዐቢይ ቀመር)፡- አምስት መቶ ሰላሳ ሁለት ዓመት ነው፡፡ ዕለት፣ ወንጌላዊ እና አበቅቴ ይገናኙበታል፡፡

ሰባቱ መስፈርታት

፩. ዕለት አንድ ዕለት ፰ ኬክሮስ

፪. ኬክሮስ አንድ ኬክሮስ ፰ ካልዒት

፫. ካልዒት አንድ ካልዒት ፰ ሣልሲት

፬. ሣልሲት አንድ ሣልሲት ፰ ራብዒት

፭. ራብዒት አንድ ራብዒት ፰ ኃምሲት

፮. ኃምሲት አንድ ኃምሲት ፰ ሳድሲት

፯. ሳድሲት ናቸው።

ከነዚህ ዓውዳት መካከል ንዑስ ቀመር ወይም ዓውደ አበቅቴ ማለት ይህ በ፲፱ ዓመት ዞሮ የሚመጣ ሲሆን በ፲፱ ዓመት አንድ ጊዜ አልቦ መጥቅዕ ወአልቦ አበቅቴ ይሆናል። ማለትም መጥቅና አበቅቴ ዜሮ የሚሆኑበት ዓመት ነው። ምክንያቱም በ፲፱ ዓመት አንድ ጊዜ ፀሐይና ጨረቃ በተፈጠሩበት ሦኅት (መስኮት) ውስጥ በተራከቦ (ተገናኝተው) የሚያድሩበት ስለሆነ ነው። አበቅቴ ፳፱ ከሆነ መጥቅ አንድ ይሆናል «ኢይኩን አሐደ መጥቅዕ ለዘመን - አንድ መጥቅዕ አትበል» የሚል አዋጅ አለን። ስለዚህ መጥቅዕ አንድ ሲሆን አበቅቴ እና መጥቅዕ አልቦ /ዜሮ/ ይሆናል።

መባጃ ሐመር

ለአጽዋማትና በዓላት ማውጫ ወሳኝ የሆነው ነጥብ መባጃ ሐመር ነው። መባጃ ሐመር መባጊያ ሐመር እየተባለም ይጠራል። መባጊያ ሐመር ሲሆን የበጋ መመላለሻ የሚል ትርጉም ይሰጣል። በሌላ በኩል መባጃ በራሱ ማቆያ፣ ማክረሚያ ተብሎ ይተረጎማል።

ሐመር መርከብ፣ መጓጓዣ የሚለውን ትርጉም ያስገኛል። መባጃ ሐመር የመጥቅዕና የዕለታት ተውሳክ ድምር ሆኖ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ቀን ያመለክታል። በሐመር የተመሰለውም አጽዋማትና በዓላት ወደ ላይና ወደታች የሚመላለሱበት ሥርዓት /መርከብ/ ስለሆነ ነው።

በአጠቃላይ መባጃ ሐመር ማለት የአጽዋማትንና የበዓላትን መዋያ ወይም መግቢያ ቀን ለማወቅ የሚያገለግል ልዩ ቁጥር ማለት ነው።

ከሰባቱ አጽዋማት መካከል አራቱ በመባጃ ሐመር መሠረት በየዓመቱ እየተቀያየሩ ወይም ቀመር እየተሠራላቸው የሚወጡ ሲሆን፣ ሦስቱ ግን ያለ መባጃ ሐመር በየዓመቱ በተመሳሳይ ወቅት ይባጃሉ።

በመባጃ ሐመር የሚባጁት አራት አጽዋማት

- ዐቢይ ጾም፣
- ጾመ ድኅነት፣
- ጾመ ነነዌና ጾመ ሐዋርያት ሲሆኑ፣

ያለ መባጃ ሐመር በየዓመቱ ቋሚ ጊዜ ይዘው የሚብቱት ሦስቱ አጽዋማት ደግሞ

- ጾመ ነቢያት፣
- ጾመ ገሃድና
- ጾመ ማርያም /ፍልሰታ/ ናቸው።

ከላይ በተመለከትነው መሠረት መባጃ ሐመር የአጽዋማትና የበዓላት ማስገኛ ልዩ ቁጥር ነው ካልን ቁጥሩ እንዴት እንደሚገኝ ማወቅ ያስፈልገናል። መባጃ ሐመርን ለማግኘት መጥቅዕንና በዓለ መጥቅዕ የዋለበትን ዕለት ተውሳክ እንደምራለን።

ተውሳክ

ተውሳክ ማለት ጭማሪ፣ ተጨማሪ ማለት ሲሆን ለበዓላትና ለአጽዋማት ማውጫ ያገለግላል። ተውሳክ ማለት ለአንድ ጾም ወይም ለአንድ ዕለት የተሰጠ ልዩ ቁጥር (ኮድ) ማለት ነው። በዚህ ቁጥር መሠረትም አጽዋማትንና በዓላትን ማውጣት ይቻላል።

መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት ነጋሪት ወይም ደወል ማለት ነው። ነጋሪት ሲመታ፣ ደወል ሲደወል ሕዝብ ይሰበሰባል፤ መልእክትም ይተላለፋል። በዓላትና አጽዋማትም በመጥቅዕ ይሰበሰባሉ፤ መዋያቸውንም በዚህ ማወቅ ይቻላል። በዚህም መሠረት መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ተደምሮ መባጃ ሐመርን ያስገኛል።

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ

«መጥቅዕ ሲበዛ ከመስከረም ንዛ፤ መጥቅዕ ሲያንስ ጥቅምትን ዳስ»

ይህ ታላቅ መልእክት ያለው የአባቶቻችን አባባል ሲሆን ለበዓለ መጥቅዕ ማውጫ የሚያገለግል ንግግራዊ ፎርሙላ ወይም ቀመር ነው፡፡ መጥቅዕ ሲበዛ ከመስከረም ንዛ ማለት በዓለ መጥቅዕን በጥቅምት አውል ማለት ሲሆን፣ መጥቅዕ ሲያንስ ጥቅምትን ዳስ ማለቱ መጥቅዕ ባነሰ ጊዜ በዓለ መጥቅዕን በጥቅምት አውለው ማለት ነው፡፡

መጥቅዕ በዛ የሚባለው ከዐሥራ አራት በላይ ሲሆን ነው፤ አነሰ የሚባለው ደግሞ ከዐሥራ አራት በታች ሲሆን ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥቅዕ ከዐሥራ አራት በላይ ከሆነ በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ይውላል፤ መጥቅዕ ከዐሥራ አራት በታች ከሆነ ደግሞ በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል፡፡ ይህ ሁል ጊዜም ቢሆን የሚያገለግል ሕግ ነው፡፡ ለዚህም ነው አበው «መጥቅዕ ሲበዛ ከመስከረምንዛ፤ መጥቅዕ ሲያንስ ጥቅምትን ዳስ» ያሉት፡፡

መባጃ ሐመርን ከመፈለጋችን በፊት ግን መጥቅዕን ማወቅ የግድ ነው፡፡ መጥቅዕን ለማወቅ ደግሞ የወንበርን ዓመታዊ ስሌት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም፤

ወንበር = ((**ቅልክ** + **ድልክ**) ፥ ፲፱) - ፭

= ((፳፯ ፭፻ + ፪፻ ፲፭) ፥ ፲፱) - ፭

= ፫፻፺፯ ቀሪ ፲ - ፭

= ፱

የ፪፻ ፲፭ ዓ.ም ወንበር ፱ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከዚህ በመነሣት መጥቅዕን ለማግኘት፤

መጥቅዕ = (**ወንበር** × ጥንተ መጥቅዕ) ÷ ፴

= (፱ × ፲፱) ÷ ፴

= ፭ ቀሪ ፳፭

= ፳፭

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ

መጥቅዕ ከዐሥራ አራት በላይ ስለሆነ መስከረም ላይ በዓለ መጥቅዕ ይውላል፡፡ ስለዚህ መስከረም ፳፭ ቅዳሜ በዓለ መጥቅዕ ሲሆን፤ ይህ በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ቅዳሜ ተውሳኩ ፯ ነው፡፡

ስለዚህ መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ

= ፳፭ + ፯

= ፴፪

የመባጃ ሐመር ዋነኛ አገልግሎት ከአጽዋማት ተውሳክ ጋር እየተደመረ በዓላትንና አጽዋማትን ማስገኘት ነው፡፡ ስለዚህ የአጽዋማትንና የበዓላትን ተውሳክ ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ በመሆኑም መባጃ ሐመሩንና የበዓላትና የአጽዋማትን ተውሳክ በመጠቀም የ፪፻ ፲፭ን የበዓላትና የአጽዋማትን መግቢያ እናገኛለን፡፡

ጾመ ነነዌ

ጾመ ነነዌ የራሱ የሆነ ተውሳክ የለውም፡፡ የሚወጣውም ያለ ተውሳክ በመባጃ ሐመር ብቻ ነው፡፡

ሀ. በዓለ መጥቅዕ በመስከረም በሚውልበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በጥር ይውላል፡፡

ለ. በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት በሚሆንበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል፡፡

ሐ. መጥቅዕ ከ፲፱ በላይ ሆኖ ከዕለት ተውሳክ ጋር ስንደምረው ከ፴ ከበለጠ ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች የማይለወጡ ቋሚ ሕጎች ናቸው፡፡

ከላይ በ«ሀ»እንደተመለከትነው በዓለ መጥቅዕ በመስከረም በሚሆንበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በጥር ይውላል ብለናል፡፡ በተጨማሪም ጾመ ነነዌ ተውሳክ ስለሌላት በመባጃ ሐመር ብቻ ነው የምትወጣ ብለናል፡፡

ስለዚህ መባጃ ሐመሩ ፳፱ ስለሆነ ጥር ፳፱ ቀን ዕለተ ሰኞ ጾመ ነነዌ ትገባለች ማለት ነው፡፡

ዐቢይ ጾም

የዐቢይ ጾምን ተውሳክ ለማግኘት ከጾመ ነነዌ ማግስት ጀምሮ እስከ ዐቢይ ጾም ያሉትን ቀናት መቁጠር ነው። እኒህም ቀናት ፲፬ ናቸው። ስለዚህ የዐቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ ይሆናል።

ዐቢይ ጾም = መባጃ ሐመር + የዐቢይ ጾም ተውሳክ

= ፷፬ + ፲፬

= ፸፰ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን።

= ፸፰ ÷ ፴

= ፪ ***ዐቢይ ጾም የካቲት ፲፫ ዕለተ ሰኑይ ይውላል።***

ደብረ ዘይት

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ዐቢይ ጾም ያሉትን ቀናት ቆጥረን የዐቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ ነው ብለናል። የደብረ ዘይትን ተውሳክ ለማግኘትም በተመሳሳይ መልኩ ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ደብረ ዘይት ያሉትን ቀናት ስንቆጥር ፸፭ ቀናትን እናገኛለን። ለ፴ ሲካፈል ቀሪ ፲፭ እናገኛለን። ስለዚህ የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፭ ይሆናል።

ደብረ ዘይት = መባጃ ሐመር + የደብረ ዘይት ተውሳክ

= ፷፬ + ፲፭

= ፸ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን።

= ፸ ÷ ፴

= ፪ ***ከየካቲት ቀጥሎ ያለው ወር መጋቢት ስለሆነ ደብረ ዘይት መጋቢት ፪ ዕለተ እሑድ ይውላል።***

ሆሣዕና

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ሆሣዕና ያሉት ቀናት ፷፪ ናቸው። ለ፴ ስናካፍለው ቀሪ ፪ እናገኛለን። ስከዚህ የሆሣዕና ተውሳክ ፪ ይሆናል።

ሆሣዕና = መባጃ ሐመር + የሆሣዕና ተውሳክ

= ፷፬ + ፪

= ፴፪ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን።

= ፴፪ ÷ ፴

= ***፪ ከመጋቢት ቀጥሎ ያለው ወር ሚያዝያ ስለሆነ በዓለ ሆሣዕና ሚያዝያ ፪ ዕለተ እሑድ ይውላል።***

ስቅለት

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ስቅለት ያሉት ቀናት ፷፯ ናቸው። ለ፴ ስናካፍለው ቀሪ ፯ እናገኛለን። በመሆኑም የስቅለት ተውሳክ ፯ ይሆናል።

ስቅለት = መባጃ ሐመር + የስቅለት ተውሳክ

= ፷፬ + ፯

= ፴፯ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን።

= ፴፯ ÷ ፴

= ***፯ በአለ ስቅለት ሚያዝያ ፯ ዕለተ ዓርብ ይውላል።***

ትንሣኤ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ትንሣኤ ያሉት ቀናት ፷፱ ናቸው፡፡ ለ፴ ስናካፍለው ቀሪ ፱ እናገኛለን፡፡ ስለዚህ የትንሣኤ ተውሳከ ፱ ይሆናል፡፡

ትንሣኤ = መባጃ ሐመር + የትንሣኤ ተውሳከ

= ፷፱ + ፱

= ፴፯ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን፡፡

= ፴፯ ÷ ፴

= ፰ በአለ ትንሣኤ ሚያዝያ ፰ ዕለተ እሑድ ይውላል፡፡

ርክበ ካህናት

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ርክበ ካህናት ያሉት ቀናት ፶፫ ናቸው፡፡ ለ፴ ስናካፍለው ቀሪ ፫ እናገኛለን፡፡ ስለዚህ የርክበ ካህናት ተውሳከ ፫ ይሆናል፡፡

ርክበ ካህናት = መባጃ ሐመር + የርክበ ካህናት ተውሳከ

= ፷፱ + ፫

= ፴፪ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን፡፡

= ፴፪ ÷ ፴

= ፪ ርክበ ካህናት ግንቦት ፪ ዕለተ ረቡዕ ይውላል፡፡

ዕርገት

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ በዓለ ዕርገት ያሉት ቀናት ፭፭ ናቸው፡፡ ፭፭ ለ፴ ስናካፍለው ፲፭ ይቀራል፡፡ ስለዚህ የዕርገት ተውሳከ ፲፭ ይሆናል፡፡

ዕርገት = መባጃ ሐመር + የዕርገት ተውሳከ

= ፷፱ + ፲፭

= ፸፬ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን፡፡

= ፸፬ ÷ ፴

= ፲፬ በአለ ዕርገት ግንቦት ፲፬ ዕለተ ሐሙስ ይውላል፡፡

፩ራቅሊጦስ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ፩ራቅሊጦስ ያሉት ቀናት ፭፲፭ ናቸው፡፡ ፭፲፭ ን ለ፴ ስናካፍለው ቀሪ ፭፭ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የ፩ራቅሊጦስ ተውሳከ ፭፭ ይሆናል፡፡

፩ራቅሊጦስ = መባጃ ሐመር + የ፩ራቅሊጦስ ተውሳከ

= ፷፱ + ፭፭

= ፻፳፬ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን፡፡

= ፻፳፬ ÷ ፴

= ፭፬ በአለ ፩ራቅሊጦስ ግንቦት ፭፬ ዕለተ ሐሙስ ይውላል፡፡

፵መ ሐዋርያት

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ፵መ ሐዋርያት ያሉት ቀናት ፻፲፱ ናቸው፡፡ ፻፲፱ን ለ፴ ስናካፍለው ቀሪ ፭፱ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የ፵መ ሐዋርያት ተውሳከ ፭፱ ይሆናል፡፡

ጾመ ሐዋርያት = መባጃ ሐመር + የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ

= ፭፬ + ፭፬

= ፺፭ ከ ፴ ስለሚበልጥ በ ፴ ገድፈን ቀሪውን እንይዛለን፡፡

= ፺፭ ÷ ፴

= ፭፭ የጾመ ሐዋርያት መግቢያ ግንቦት ፭፭ ዕለተ ሰኞ ይውላል፡፡

ጾመ ድኅነት

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ጾመ ድኅነት ያሉት ቀናት ፻፳፭ ናቸው፡፡ ፻፳፭ ለ፴ ሲካፈል ቀሪ ፭ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፭ ይሆናል፡፡

ጾመ ድኅነት = መባጃ ሐመር + የጾመ ድኅነት ተውሳክ

= ፭፬ + ፭

= ፴ የጾመ ድኅነት መግቢያ ግንቦት ፴ ዕለተ ረቡዕ ይውላል፡፡

ኢየዐርግና ኢይወርድ

እነዚህ አጽዋማት ምንም እንኳን በየዓመቱ የየራሳቸው ቀመራዊ ማውጫ ቢኖራቸውም ገደብ ግን አላቸው፡፡ ገደባቸውም በግእዝ ኢይወርድና ኢየዐርግ ሲባል፣ ኢይወርድ የታችኛው እርከን፣ ኢየዐርግ ደግሞ የላይኛው እርከን ነው፡፡ በአማርኛው ገደብ ልንለው እንችላለን፡፡ በዚህም መሠረት የአጽዋማት ገደብ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ተ.ቁ	አጽዋማትና በዓላት	ኢይወርድ	ኢየዐርግ
፩.	ጾመ ነነዌ	ጥር ፲፭	የካቲት ፭፩
፪.	ዐቢይ ጾም	የካቲት ፭	መጋቢት ፭
፫.	ደብረ ዘይት	የካቲት ፳፭	ሚያዝያ ፪
፬.	ሆሣዕና	መጋቢት ፲፱	ሚያዝያ ፳፫
፭.	ስቅለት	መጋቢት ፳፬	ሚያዝያ ፳፰
፮.	ትንሣኤ	መጋቢት ፳፮	ሚያዝያ ፴
፯.	ርክበ ካህናት	ሚያዝያ ፳	ግንቦት ፳፬
፰.	ዕርገት	ግንቦት ፭	ሰኔ ፱
፱.	ጰራቅሊጦስ	ግንቦት ፲፭	ሰኔ ፲፱
፲፩.	ጾመ ሐዋርያት	ግንቦት ፲፮	ሰኔ ፳
፲፪.	ጾመ ድኅነት	ግንቦት ፲፰	ሰኔ ፳፪